# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ማስፈፀምያ መመሪያ ቁጥር 43/2013

ነሓሴ 2011 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION TRANSPORT BUREAU

## መግቢያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ በከተማው የአስተዳደር ወሰን ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሞተር ብስክሌቶች በከተማው ነዋሪና የትራፊክ እንቅስቃሴ ላይ የሚፈጥሩትን አላስፈላጊ ተፅዕኖ ለመቀነስ በሞተር ብስክሌት ፈቃድና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 02/2011 መሰረት የፈቃድና ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱ ይታወቃል።

ስለሆነም ይህ መመሪያ ተግባራዊ ሲደረግ የተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች በአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት ቢሮ ተጠሪ ተቋማት የተሽከርካሪ ሰሌዳ የወሰዱ እንዳሉ ይታወቃል። በከተማዋ በሞተር ብስክሌት የሚደረግ እንቅስቃሴ በመገደቡ ምክንያት እነዚህ የማህበረሰቡ አካላት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር እንዳያስከትል ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይህንን ችግር ለመቅረፍ የቁጥጥር ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ አገልግሎቱ ህጋዊ አደረጃጀትና ፍቃድ ኖሮት ማስቀጠል የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት አስፈገላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የሞተር ብስክሌት የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጅ በማስገጠም በማህበር በመደራጀትም በግል የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባራትን ለማከናወን ፈቃድ የሚጠይቁ አካላትን ለማስተናገድ ዝርዝር የአሰራር መመሪያ እንደሚያዘጋጁ ኃላፊነት የሚጥል በመሆኑና የሚገጠመውን የሞተር ብስክሌት መከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጅ ዝርዝር መግለጫ (Specification) በመመሪያ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአዲስ አበባ አስተዳደር በከተማው ውስጥ መንገደኞች፣ እቃዎች፣ በንግድ ትራንስፖርት ስለሚጓጓዙበት ሁኔታ መመሪያ ማውጣትና አፈጻጸሙን መከታተል እንዲችል በፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን በተሰጠው ውክልና መሠረት በአዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀፅ 3(ሠ) በሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥበትን አደረጃጀትና አሰራር ለመወሰን ይህን መመሪያ አውጥቷዋል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ *"በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ማስፈፀምያ መመሪያ ቁጥር*43/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

2.2. **"አስተዳዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

2.3. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤

2.4. **"ኤጀንሲ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ነው፤

2.5. **"ባለስልጣን** ማለት የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው፤

2.6. **"ኦፕሬተር"** ማለት የንግድ የሞተር ሳይክል ተሽከርካሪ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ተመዝግቦ የሙያ ብቃት የተሰጠው የተሽከርካሪ ባለንብረት ወይም ድርጅት ወይም ሠራተኞችን ነው፤

2.7. **"የብቃት ማረጋገጫ"** ማለት በአዲስ አበባ ትራንስፖርት ባለስልጣን በሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ለሚሰማሩ ማኅበራትና ድርጅቶች የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው፤

2.8. **"ተጠቃሚ"** ማለት የሞተር ብስክሌት መከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጅ (GPS) በማግጠምና ፈቃድ በመውሰድ በግለሰብ፣ በድርጅትና በማህበር ስም በተመዘገቡ ሞተር ብስክሌቶች አማካኝነት በከተማው ውስጥ ለመንቀሳቀስ የሚቀርብ ግለሰብ ወይም ኦፐሬተር ማለት ነው፤

2.9. **"የሞተር ብስክሌት መከታተያ ስርዓት"** ቴክኖሎጂን በመጠቀም የአንድን ሞተር ብስክሌት መረጃ በማስተላለፍ የሞተር ብስክሌቱን እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችል ቴክኖሎጂ ነው፤

2.10. **"ተቆጣጣሪ"** ማለት የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎችንና የትራንስፖርት ህጎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር አግባብነት ባለው ሕግ ሥልጣን የተሰጠው የባለስልጣኑ ወይም አግባብነት ባለው አካል የተመደበ ወይም የፖሊስ አባል ነው፤

2.11. **"ማህበር"** ወይም ድርጅት ማለት የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰዱ ባለንብረቶች ወይም ኦፕሬተሮች የሚያቋቁሙት ማኅበር ወይም ድርጅት ነው፤

2.12. **"የማህበር ፈቃድ"** ማለት የንግድ ቢሮ ወይም የንግድ ሚኒስቴር ወይም ሌላ ማህበራትን ለማደራጀት ስልጣን ባለው አካል የተመዘገቡ በማኅበር ተደራጅተው የንግድ የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ለወሰዱ ባለሀብቶች የሚሰጥ የማኅበር ምዝገባ ፈቃድ ነው፤

2.13. **"የድርጅት ፈቃድ"** ማለት ከንግድ ቢሮ ወይም ከንግድ ሚኒስቴር በሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስማራት እንዲቻል የሚሰጥ የንግድ ፈቃድ ነው፤

2.14. **"የትራንስፖርት አገልግሎት"** ማለት በሞተር ብስክሌት አማካኝነት የሚሰጡ መንገደኞችን ወይም ዕቃዎች የማጓጓዝ አገልግሎት ማለት ነው፤

2.15. **"የፍጥነት ወሰን"** ማለት በዚህ መመሪያ የተደነገጉ የሞተር ብስክሌት እንቅስቃሴ የሚገድብ ጣሪያ የአሽከርክሪት ፍጥነት ነው፤

2.16. **"ብራንድ"** ማለት አንድን ተቋም ወይም ድርጅት በተለየ መልኩ የሚገልፅ የቀለም ቅብ እና ስዕላዊ መግለጫ ማለት ነው፤

2.17. **"አርማ"** ማለት አንድን ድርጅት ወይም ተቋም በልዩ ሁኔታ የሚገልፅ ስዕላዊ ምልክት ወይም ፅሁፍ ሆኖ በሚመለከተው የመንግስት አካል ህጋዊ እውቅና ያለው ነዉ፤

2.18. **"ዩኒፎርም"** ማለት የአንድን ተቋም ወይም ድርጅት ሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ በተለየ መልክ የተዘጋጅ ሙሉ ልብስ ነው፤

2.19. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።



በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION TRANSPORT BUREAU አአትቢ AATB

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተመዝግበው በሚገኙ ነባር የሞተር ብስክሌቶች እና የትራንስፖርት አገልግሎት ፍቃድ በሚሰጣቸው ግለሰቦች፣ ማህበራት እና ድርጅቶች ላይ ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል።

## 4. የፆታ አገላለፅ

በዚህ መመሪያ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ የሴትንም ይጨምራል።

# ክፍል ሁለት

# የሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነቶችና አደረጃጀት

## 5. በሞተር ብስክሌት ሊሰጡ የሚችሉ የትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነቶች

በሞተር ብስክሌት አገልግሎት የሚሰጡ የትራንስፖርት አገልግሎት አይነቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

5.1. መንገደኞችን በክፍያ ከቦታ ቦታ ማዘዋወር፤

5.2. በሞተር ብስክሌቱ በተገጠመ የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን ውስጥ የተለያዩ እቃዎችንና መልእክቶችን በክፍያ ማመላለስ፤

5.3. ለግል የትራንስፖርት አገልግሎት ፍላጎት መጠቀም፤

## 6. የትራንስፖርት አገልግሎት ፈቃድ የሚያገኙ የሞተር ብስክሌቶች በተመለከተ

6.1 በከተማው ውስጥ የሞተር ብስክሌት ምዝገባ በማካሄድ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ የሞተር ብስክሌት ባለንብረቶች በማህበር በመደራጀት በሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰማሩ በባለስልጣኑ ፈቃድ ይሰጣቸዋል።

6.2 በማህበር በመደራጀት በትራንስፖርት አገልግሎት ለመሰማራት ፈቃድ የሚሰጣቸው ሞተር ብስክሌቶች በኮድ-3 የተመዘገቡ ብቻ ይሆናሉ።

6.3 በአዲስ አበባ ከተማ ያልተመዘገቡ የሞተር ብስክሌቶች በከተማው ውስጥ በትራንስፖርት አገልግሎት ለመሰማራት ፈቃድ ሊሰጣቸው አይችሉም።

6.4 በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለመንቀሳቀስ በኮድ-2 ተመዝግበው የሚገኙ ሞተር ብስክሌቶች ሰሌዳቸውን ወደ ኮድ-3 በመቀየር በትራንስፖርት አገልግሎት ለመሰማራት ይፈቀድላቸዋል።

6.5 በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለግል ትራንስፖርት አገልግሎት ለማዋል በኮድ-2 የተመዘገቡ ሞተር ብስክሌቶች በስሙ በተመዘገበ ግለሰብ ብቻ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል።

6.6 ማንኛዉም ባለ ኮድ-2 ሞተር ብስክሌት ከአሽከርካሪው ውጭ ተጨማሪ ሰው መጫን በዚህ መመሪያ የተከለከለ ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION TRANSPORT BUREAU
AA TB

6.7 በከተማው የሞተር ብስክሌት ምዝገባ በአዲስ ሁኔታ በመመዝገብ ወይም በዝውውር ከሌሎች ክልሎች በማስተላለፍ በአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ላይ ሞተር ብስኪሌቶች ለማንቀሳቀስ በኮድ-3ም ሆነ በኮድ-2 ፈቃድ ሊሰጣቸው አይችልም።

## 7. በሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ለማግኘት ሊሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶች

7.1 በሞተር ብስክሌቱ ላይ የመከታተያና መቆጣጠሪያ ስርዓት ቴክኖሎጂ አስገጥሞ የሚቀርብና ኤጀንሲው ፍቃድ ከሰጣቸው የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ውል የፈጸመ የሆነ፤

7.2 በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 5.1 እና 5.2 የተጠቀሱትን አገልግሎቶች ለመስጠት፤

7.3 በባለስልጣኑ እውቅና ያለው ማህበር አባል መሆን፤

7.4 የሞተር ብስክሌት ኮድ-3 ካልሆነ ወደ ኮድ-3 ለመቀየር ፍቃደኛ መሆን፤

7.5 ማንኛዉም ቀለም መቀባት የሚችል የሞተር ብስክሌቱ አካል በሰማያዊና ነጭ 6ሳ.ሜ. በ6ሳ.ሜ. ዳማ ለሰዉ ማመላለስ የሚሰራ ከሆነ በብጫና ሰማያዊ 6ሳ.ሜ. በ6ሳ.ሜ. ዳማ ለየመልእክት ተላላኪ የሚሰራ በማይለቅ ቀለም መቀባት፤

7.6 ለሰው ማመላለስ የሚሰራ ከሆነ በሰማያዊና ነጭ 6ሳ.ሜ. በ6ሳ.ሜ. ዳማ ቀለም ዩኒፎርም ማዘጋጀት፤

7.7 ለመልእክት ማመላለስ የሚሰራ ከሆነ በብጫና ሰማያዊ 6ሳ.ሜ. በ6ሳ.ሜ. ዳማ የተዘጋጀ ዩኒፎርም ማዘጋጀት፤

7.8 በባለስልጣኑ የተመረጠውን የአሽከርካሪ ዩኒፎርም እና መለያ መታወቂያ ማዘጋጀት፤

7.9 በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ጠብቆ ለመንቀሳቀስ ፈቃደኛ የሆነ፤

# ክፍል ሦስት

# የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ ዓይነት ስለመወሰን

## 8. የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ ዝርዝር መግለጫ (Specification)

በሞተር ብስክሌቶች ላይ የሚገጠመው የመቆጣጠሪያ እና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ (GPS) ዝርዝር መግለጫ (Specification) ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ዋና ዋና ነጥቦች ማሟላት ይገባቸዋል፡-

8.1 በየትኛውም ሰዓትና ጊዜ የሞተር ብስክሌቱ ያለበትን ቦታ እና ሁኔታ (Real-time) በግልፅ ሊያሳይ የሚችል መሆን አለበት፤

8.2 በኤጀንሲው እውቅና ከተሰጠው የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ አቅራቢ ድርጅት የመቆጣጠሪያ ስርዓት (System) ጋር የተጣጣመ ሊሆን ይገባል፤

8.3 ሞተር ብስክሌቱ ቢያንስ ሲሄድበት የነበረውን ፍጥነት፣ የተቀንሳቀሰበትን ቀን፣ ሰዓት፣ ዓመተ ምህረት እንዲሁም የተንቀሳቀሰበትን አካባቢ ትክክለኛ መረጃ እንዲሁም የነበረበትን ቦታ ማሳየት የሚችልና መስጠት የሚችል መሆን ይገባዋል፤

8.4 ሞተር ብስክሌቱ በቀላሉ የሚለይበት የራሱ የሆነ የተለየ የመለያ ቁጥር እና ሌሎች መለያ ኮዶች የያዘ መሆን ይገባዋል፤



በአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት ቢሮ
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION TRANSPORT BUREAU
አ.አ.ት.ቢ. AATB

8.5 ቴክኖሎጂ ቢያንስ በሀገሪቱ ያለውን ዝቅተኛ የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ መስፈርት ያሟላ መሆኑን ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ሊኖረው ይገባዋል፤

8.6 የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂው የሞተር ብስክሌት ተጠቃሚ ሞተር ብስክሌቱ የተንቀሳቀሰበትን እና ያልተንቀሳቀሰበትን ቀን፣ ሰዓት እና ዓመተ ምህረት ትክክለኛ መረጃ መስጠት የሚችል እንዲሁም ሲሄድበት የነበረበትን ፍጥነት ትክክለኛ መረጃ መስጠት የሚችል መሆን ይገባዋል፤

8.7 እያንዳንዱን መረጃ የሞተር ብስክሌቱን ሙሉ እንቅስቃሴ በማያቋርጥ ሁኔታ በግልፅ የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፤

8.8 በተለያዩ ምክንያቶች የኃይል መቆራረጥ ቢያጋጥም ወይም ጉዳት ለማድረስ ቢሞከር ቢያንስ ለአንድ ሰአት ያህል የሞተር ብስክሌቱን ሙሉ እንቅስቃሴ የሚያሳይ እና ማሳወቅ የሚችል መሆን አለበት፤

8.9 ከፍተኛ የፍጥነት ወሰን 40 ኪ/ሜ በሰዓት በላይ ሲያሽከረክር የቀይ መብራት ማሳየት የሚችል ሆኖ የፍጥነት ወሰኑን ሲያልፍ ቢያንስ ከ 5 ሰከንድ ቆይታ በኃላ ያለማቋረጥ ቀይ መብራት ምልክት በጉልህ እንዲያሳይ ሆኖ የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል፤

8.10 ማንኛውም ማህበር ወይም ድርጅት ከኤጀንሲው ውል ከገባባቸው ቴክኖሎጅ አቅራቢ ተቋማት ጋር ብቻ ውል መያዝ አለበት፤

8.11 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ የሞተር ብስክለተቶች የጥፋት አመላካች ቀይ መብራት ከማዕከል በመሆን ቀይ እንዲበራ ወይም እንዲጠፋ ማድረግ የሚችል መሆን አለበት፤

8.12 በማንኛውም ሰዓት አሽከርካሪው በሞተር ብስክሌቱ ቀይ በርቶ ሲያገኝ ለኤጀንሲው ስልክ በመደወል እንዲጠፋለት ማድረግ የሚችልበት አሰራር የዘረጋ።

## ክፍል አራት

## ተግባርና ኃላፊነት

### 9. የትራንስፖርት ባለስልጣን ተግባርና ሀላፊነት

9.1 በየዓመቱ በከተማዋ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ የሞተር ብስክሌቶች ዓመታዊ የቴክኒክ ብቃት ሠርትፍኬት በሎ ሲያቀርቡ ምዝገባ በማከናወን ፍቃድ ያድሳል።

9.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9.1 መሠረት በየዓመቱ የምዝገባ ፍቃድ ያላሳደሰ ማህበር ወይም ድርጅት ወይም የሞተር ብስክሌት ባለቤት የትራንስፖርት አገልግሎት እንዳይሰጥ ይከለክላል፣ ለተፈጻሚነቱም ይቆጣጠራል።

9.3 የሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት የክፍያ ታሪፍ መጠን እና የስምሪት መስመር እንደአስፈላጊነቱ በጥናት ሊወስን ይችላል።

9.4 የአገልግሎት አሰጣጡ በየወቅቱ በመከታተል፣ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ አስፈላጊ አቅጣጫዎችን ይሰጣል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል።

9.5 በትራንስፖርት አገልግሎት ማህበር የተደራጀ ማንኛዉም አባል ወደ ሌላ ማህበር ጋር ለመደራጀት ቢፈለግ ከዚህ በፊት የትራንስፖርት አገልግሎት ከሚሰጥበት ማህበር ሕጋዊ መሸኛ ደብዳቤ (Clearance) ሲያቀርብ ዝውውሩን ይፈቅዳል።

9.6 ዓመታዊ የምዝገባ እና የፍቃድ እድሳት ተግባራት በመመዘኛ መስፈርት (ቼክ ሊስት) መሰረት ያከናውናል እንዲሁም የአገልግሎት የቅሬታ አፈታት ስርዓት ይዘረጋል።

9.7 የሙያ ማሻሻያ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያዘጋጃል፣ ያከናውናል።

9.8 የቁጥጥር ሰራተኞች በከተማዋ መንገድ ላይ በማሰማራት ወይም በትራፊክ ፖሊስ አማካኝነት የሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት ስራ ላይ የቁጥጥር ተግባር ያከናውናል፣ ጥፋት ተፈፅሞ ሲያገኝም ተቆጣጣሪው ወዲያውኑ የክስ ቻርጅ ወረቀት በመሙላት ለተከሳሹ አስፈርሞ ይሰጣል።

9.9 በቁጥጥር ወቅት ህጋዊ ማስረጃዎች ያልያዙ እና በህገወጥ መንገድ አገልግሎት ሲሠጥ የተገኘን የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪውን የማሰር እና በህግ ፊት በማቅረብ በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ መሠረት እንዲቀጣ የማድረግ ሀላፊነት አለበት።

## 10. የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት

10.1 በሞተር ብስክሌቶች ላይ የተገጠሙ የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂዎችና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂዎች በተቀመጠው ዝርዝር መግለጫ (Specification) መሠረት መሆኑን ማረጋገጥ፤

10.2 ተገቢውን ግዴታ እንዲገቡ በማድረግ ፈቃድ እንዲያገኙ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ፤

10.3 የመከታተያ ስርዓቱን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ፈቃድ በወሰዱ አካላት ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፤

10.4 የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ ለሚያስፈልጋቸው ተጠቃሚዎች የመጠቀም ፈቃድ መስጠት፤

10.5 የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጅ ተጠቃሚዎች ቴክኖሎጂውን በሚያሽከረክሩት ሞተር ብስክሌት ላይ በአግባቡ በመግጠም በከተማዋ ሰላማዊ በሆነ መልኩ መንቀሳቀሳቸውን እንዲሁም በከተማዋ ለማሽከርከር በተፈቀደው የፍጥነት ወሰን እያሽከረከሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

10.6 የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ ዕቃዎችን ዓይነት፣ ባለቤት፣ ቦታና የመሳሰሉትን መረጃዎች የያዘ መረጃ እንዲደራጅ ማድረግ፤

10.7 ሞተር ብስክሌት በመጠቀም የትራፊክ ህጎችና ሌሎች የህግ መተላለፎች ሲፈፀሙ ቴክኖሎጂውን በመጠቀም መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል ማቅረብና ባለው ስልጣን እርምጃ መውሰድ።

## 11. የሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ማህበር ወይም ድርጅት ኃላፊነት

11.1 በሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት በትራንስፖርት ባለስልጣን የተሰጠው ፈቃድ በማንኛውም ዓይነት እንቅስቃሴ መያዝ እና በተቆጣጣሪ ሰራተኞች (ትራፊክ ፖሊስ) መረጃውን ሲጠየቁ ፈቃዱን የማሳየት፤

11.2 ማንኛውም የሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ፈቃድ ሳይወስዱ አገልግሎት አለመስጠት፤

11.3 የኦፕሬተሩ ፍቃድ የሚቀየር ከሆነ ሥራ ከማቆሙ በፊት ከ15 ቀን በፊት የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ለሰጠው አካላት ማሳወቅ፤

11.4 የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች አዲስም ሆነ ሲጠገን በዚህ መመሪያና በሌላም ሕግ ከተቀመጠው መስፈርት ውጪ ሲሆን አግባብነት ላለው አካል ማሳወቅ፤

11.5 አግባብነት ካለው አካል በልዩ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ማኅበር እና ድርጅት ከተፈቀደለት የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪዎች ዝርዝርና ብዛት ውጭ አለማሳተፍ፤

11.6 ደህንነቱ እና ምቾቱ የተጠበቀ የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪ ለሚሰጠው አገልግሎት የማቅረብ፤

11.7 ለአገልግሎት የሚውሉ የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪዎች የወቅቱን ሙሉ ኢንሹራንስ ያላቸው መሆኑን የማረጋገጥ፤

11.8 ተገልጋዩ ያለበትን ግዴታና መብቱን የማሳወቅ እና ተፈፃሚነቱን የመከታተልና የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፤

11.9 በራሳቸው ወጪ የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጅ መሳርያና መሰርያው የሚልከውን መረጃ መከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጅ ማስገጠም፤

11.10 በራሳቸው ወጪ ከመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂው በተጨማሪ የሞተረኛውን አግባባዊ የፍጥነት እንቅስቃሴ የሚያሳይ መብራት (speed indicator) አብሮ ማስገጠም፤

11.11 ኤጀንሲው ካረጋገጠውና ፍቃድ ከሰጣቸው እንዲሁም ከኤጀንሲው ጋር ግዴታ ከገቡ የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጅ አልሚዎች ጋር ብቻ ውል በመግባት ፈቃድ ማግኘት፤

11.12 ተጠቃሚው ፈቃድ ሲያገኝ በሰጠው አድራሻ መሠረት ለማንኛውም ጉዳይ በኤጀንሲውም ሆነ በባለስልጣኑ ሲፈለግ የመቅረብና የአድራሻ ለውጥም ካደረገ የማሳወቅ ኃላፊነት ይኖርበታል።

## 12. የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ አቅራቢ ድርጅቶች ኃላፊነት

12.1. የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂን የሚያቀርበው ተቋም በሀገሪቱ የንግድ ህግ መሠረት የተመዘገበና የታደሰ ፈቃድ ያለው እንዲሁም ከኤጀንሲው ጋር የግዴታ ውል መግባት የሚችል መሆን አለበት፤

12.2. የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂን የሚያቀርበው ተቋም የሀገሪቱን የመረጃ ደህንነት ጠብቆ የሚሰራ መሆን አለበት፤

12.3. የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጅን የሚያለማው ተቋም ለኤጀንሲው ማንኛውንም የሞተረኛውን መረጃ ማቅረብ የሚችል መሆን ይገባዋል፤

12.4. የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂን የሚያለማው ተቋም ከሞተር ብስክሌት ተጠቃሚ ጋር በተያያዘ የሚያገኘውን ማንኛውንም መረጃ ከውሉ ውጭ መጠቀም አይችልም፤

12.5. መከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂን የሚያለማው ተቋም ከሞተር ተጠቃሚ ጋር በተያያዘ የሚያገኘውን ማንኛውንም መረጃ ቢያንስ ለአንድ ዓመት መያዝ የሚችል የመረጃ ቋት ሊኖረውና ሙሉውን መረጃ ለኤጀንሲው በተፈለገው ጊዜ ማቅረብ የሚችል መሆን ይገባዋል፤

12.6. ውል ያስገባውን የሞተር ብስክሌት ተጠቃሚ በውሉ መሠረት መቆጣጠር ካልቻለ ውል የገቡ ተጠቃሚዎችን ያለ ምንም ተጨማሪ ክፍያ ወደ ሌላ በኤጀንሲው እውቅና ለተሰጠው ተቋም ያዛውራል፤

12.7. ከሞተር ብስክሌት ተጠቃሚዎች ጋር ውል ሲገባ በዚህ መመሪያ የተፈቀደውን የፍጥነት ወሰን አክብሮ እንዲንቀሳቀስ ግዴታ ያስገባዋል፤ ከፍጥነት ወሰን በላይ ሲያሽከረክርም ምልክት ለኤጀንሲው እንደሚሰጥ በማድረግ ሊያሳውቀው ይገባል፤



ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION TRANSPORT BUREAU

12.8. ኤጀንሲው የሚፈልጋቸውን መረጃዎች ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በተጠየቀ ጊዜ ሁሉ ማቅረብ ይኖርበታል፤

12.9. የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂው ሁልጊዜ ስራ ላይ መሆኑን ማረጋገጥ፤

12.10. በገባው ግዴታ መሠረት ለኤጀንሲው መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂውን የማየትና መረጃ የማግኘት መብት መስጠት፤

12.11. የመጠቀሚያ ፈቃዱን በወቅቱ የማደስ፤

12.12. የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ ከመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጅ ጋር ሳይገጥሙ በከተማዋ የተለያዩ ቦታዎች ላይ አለመንቀሳቀስ፤

12.13. በኤጀንሲው ፍላጎት መሰረት በየትኛውም ጊዜ በመቅረብ ተገቢ መረጃ መስጠት፤

12.14. እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር ከሚያስችለው ስርዓት (System) ጋር የሚናበብ እና ስርዓቱ (System) ተቀባይነት ያለው የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂን ብቻ መጠቀም፤

12.15. የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ ዕቃዎች ላይ ያለውን መለያ ኮድ አለማጥፋት ወይም አለመቀየር፤

12.16. የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጅ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ከኤጀንሲው እውቅናና ፈቃድ ውጪ ከተገጠመበት ቦታ አለመቀየር፤

12.17. በማንኛውም ሁኔታ የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጅ አለማጥፋት ወይም አለማበላሸት፤

12.18. የተገጠመው የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጅ ላይ ብልሽት ሲጋጥም ብልሽቱን በፍጥነት ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ።

## ክፍል አምስት

## ስለ አቤቱታ

### 13. ስለ አቤቱታ አቀራረብ

በዚህ መመሪያ መሠረት በተወሰደው እርምጃ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው:-

13.1 እርምጃው በተወሰደ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለሚመለከተው ባለስልጣኑ ወይም ኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ በፅሁፍ ማቅረብ ይችላል፤

13.2 የባለስልጣን ወይም የኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ አቤቱታው በቀረበለት በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን መርምሮ ውሳኔ መስጠት አለበት፣ ውሳኔውንም በጽሁፍ አድርጎ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፤

13.3 ባለስልጣኑ ወይም ኤጀንሲው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ወይም ኤጀንሲው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልተሰጠው ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ወይም ውሳኔ መስጠት ከነበረበት ቀን አንስቶ በአምስት የሥራ ቀናት አቤቱታውን ለቢሮው ማቅረብ ይችላል።

ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION TRANSPORT BUREAU

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14. የስራ ልብስ (ዩኒፎርም)

14.1 በከተማዋ የሰው እና የዕቃ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ሞተር ብስክሌት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 መሰረት እንደየስራ ዘርፋቸው አንድ ዓይነት የሆነ የስራ ልብስ (ዩኒፎርም) ይለብሳሉ፡፡

14.2 ዩኒፎርሙ በሌላ መደበኛ ልብስ ላይ በመደረብ የሚለበስ ቀላልና ከፊት እና ከኃላው የዳማ ቀለም (የቼዝ መጫወቻ) ዓይነት ሲሆን የምሽት አንፀባራቂ በአግድም የተለጠፈበት ሆኖ፡-

i. የዳማው ቀለም ሰማያዊና ነጭ ለሰዉ ማመላለስ ለሚሰሩ ቢጫና ሰማያዊ ለመልእክት ማመላለስ ለሚሰረሩ ሆኖ መጠኑ 6ሳ.ሜ. በ 6ሳ.ሜ. የሆነ፤

ii. ከጀርባዉ የሞተር ብስክሌቱ ሰሌዳ ቁጥር በጥቁር-ሰማያዊ መደብ በነጭ ቀለም ለሰው ማመላለስ የሚሰሩ የተለጠፈና በጥቁር-ሰማያዊ መደብ በቢጫ ቀለም የሆነ እና የቁጥሮቹ መጠኑ 10 ሳ.ሜ. የሆኑ፤

iii. ከፊቱ በስተግራ ደረት የአሽከርካሪዉ ማንነት የሚገልፅ ማስቀመጫ የሚያሳይ ኪስ ያለው፤

iv. የሰዉ ማመላለስ የሚሰሩ አሽከርካሪዉም የተሳፋሪውም ሄልሜት ነጭ የሆነ፤

v. የመልእክት ማመላለስ የሚሰሩ የአሽከርካሪው ሄልሜት ቢጫ የሆነ

### 15. የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን

15.1 ዕቃ የሚያመላልሱ ሞተር ብስክሌቶች ዕቃውን የሚይዙበት ሳጥን 50 ሳ.ሜ x 46 ሳ.ሜ x 46 ሳ.ሜ ያልበለጠ መጠን እንዲሁም ዝናብ በማያስገባ ሁኔታ በብረት ወይም በፕላስቲክ የተሰራ መሆን አለበት፡፡

15.2 የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን ተመሳሳይ እይታ እንዲኖረው እነደ ሞተር ብስክልቱ ቀለም ቢጫና ሰማያዊ 6ሳ.ሜ. በ 6ሳ.ሜ. ዳማ በሆነ በማይለቅ ቀለም መቀባት አለበት፡፡

### 16. ሄልሜት

16.1 የሞትር ብስክሌት አሽከርካሪ ደህንቱን ለመጠበቅ የሚረዱ ሄልሜት እና ሌሎች የደህንነት መጠበቅያ መሳሪያዎች መጠቀም አለበት፡፡

16.2 ማንኛውም ሞተር ብስክሌት ሰው በሚያሳፍርበት ጊዜ የተሳፋሪውን ደህንነት የሚያረጋግጥ ሄልሜት ማድረግ ይገባል፡፡

### 17. የፍጥነት ወሰን

በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር የከተማዋ የሞተር ብስክሌት የፍጥነት ወሰን 50 ኪ/ሜትር በሰዓት ነው፡፡

## 18. የተከለከሉና ቅጣት የሚያስከትሉ ተግባራት

18.1 ማንኛውም የሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት አሰጣጥ ላይ የሚዉሉ ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ መመሪያ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ሳይኖረው አገልግሎት መስጠት፤

18.2 ማንኛውም የሞተር ብስክሌት አገልግሎት ሰጪ ማህበር፣ ድርጅት ፈቃዱን አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን፤

18.3 ማንኛውም ኦፕሬተር ፈቃድ በተሰጠበት ወቅት ተሟልተዋል በሚል ያሳያቸው መመዘኛዎች በቁጥጥር ወቅት ተሟልተው አለመገኘት፤

18.4 አግባብነት ካለው አካል ካልተፈቀደ በስተቀር የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪው ከተፈቀደለት የአገልግሎት ዓይነት ውጭ እንዲሠማራ በማድረግ የትራንስፖርት አገልግሎት አሠጣጥ ላይ መገኘት እና አፈፃፀሙን ማዛባት፤

18.5 በዚህ መመሪያ የወጣውን መመዘኛ ያላሟሉ በተለያዩ የዲሲፒሊን ጉድለት ምክንያት የተቀጡ እና የታገዱ የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪዎችን መቅጠር፤

18.6 በሥራ ላይ እያለ አግባብ ባላቸው የክትትል፣ የድጋፍና ቁጥጥር ሠራተኞች ወይም ሌሎች ሕጋዊ አካላት ማንኛውም ዓይነት መረጃ ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን፤

18.7 በኦፕሬተሮች መካከል የሚደረግ ማንኛውም ውድድር የትራንስፖርት ዘርፉን በሚጎዳ ሁኔታ እንቅስቃሴ ማድረግ፤

18.8 የመጠቀሚያ ፈቃዱን በወቅቱ አለማደስ፤

18.9 የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ ከመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጅ ጋር ሳይገጥሙ በከተማዋ የተለያዩ ቦታዎች ላይ መንቀሳቀስ፤

18.10 የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጅ ዕቃዎች ላይ ያለውን መለያ ኮድ ማጥፋት ወይም መቀየር፤

18.11 የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጅ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ከኤጀንሲው እውቅናና ፈቃድ ውጪ ከተገጠመበት ቦታ መቀየር፤

18.12 በማንኛውም ሁኔታ የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጅ ማጥፋት ወይም ማበላሸት።

## 19. ስለ ቅጣት

19.1 በሌላ ሕግ ወይም በሞተር ብስክሌት ፈቃድና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 2/2011 የተጣሉ ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 14 የተከለከሉ ተግባራትን የፈፀሙ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ የወሰዱ ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና ማህበራት ለመጀመሪያ ጊዜ 500 ብር እንዲቀጡ ይደረጋል።

19.2 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በተወሰደ እርምጃ ባለመስተካከል ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት የፈፀመ አካል 1000 ብር ተቀጥቶ የተሰጠው ፈቃድ ለ3 ወር ይታገዳል።

## 20. የመተባበር ግዴታ

ይህንን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የትራንስፖርት ድርጅቶች፣ ማህበራትና ግለሰቦች የመተባበር ግዴታ አለባቸዉ።



በአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት ቢሮ
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION TRANSPORT BUREAU
አአትቢ AATB

**21. ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ሕጐች**

ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር ይህን መመሪያ የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**22. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህን መመሪያ በሙሉ ወይም በከፊል በማንኛውም ጊዜ ቢሮው ሊያሻሽለው ይችላል።


**23. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ የአፈፃፀም መመሪያ ከነሐሰ 16፣ 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።


አዲስ አበባ

ነሓሴ 16 ቀን 2011ዓ.ም.

ሰለሞን ኪዳኔ ዘገየ (ፒ.ኤች.ዲ.)
የአዲስ አበባ ከተማ ኢኮኖሚ ክላስተር አስተባባሪና
የትራንስፖርት ቢሮ ሀላፊ




የሰው ማመላለሻ ሞተር ብስክሌት ቀለም።




የሞተር ሳይክል ትራንስፖርት አገልግሎት ደምብ ልብስ




ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION TRANSPORT BUREAU



የመልእክት ማመላለሻ ሞተር ብስክሌት ቀለም።

በአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት ቢሮ
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION TRANSPORT BUREAU
AATB




የሞተር ሳይክል ተለላኪ አገልግሎት ደምብ ልብስ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION TRANSPORT BUREAU